CITY OF ALEXANDRIA • VIRGINIA •

T&ES
TRANSPORTATION &
ENVIRONMENTAL SERVICES

# የአገልግሎቶች መመሪያ

## 2025



እንደገና መጠቀም • እንደገና ጥቅም ላይ ማዋል
ቆሻሻ • አንጸባራቂ • ብረት • በሰም የተሸፈነ • ዝርግ
ለስላሳ ወረቀት • የወረቀት ቱቦ • የወረቀት ሣጥን

# ማውጫ


ስለ T&ES የኃብት መልሶ ማግኛ ክፍል 3

ሳምንታዊ የአሰባሰብ አገልግሎቶች 4

መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል 6

የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋል መጣያ ማዕከላት 8

መስታወት 9

መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል በልዩ ክንውኖች ቦታ 10

የጋራ ቦታ መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል 11

የጓሮ ቆሻሻ 12

የቅጠል አሰባሰብ 13

ኦርጋኒኮች 15

በገበሬ ገበያዎች የምግብ ትርፍራፊ ወደማዳበሪያ መቀየር 16

የቆሻሻ አገልግሎቶች 17

ከቤት የሚወጣ አደገኛ ቆሻሻ እና ኤሌክትሮኒክስ 19

ባትሪዎች 21

የፕላስቲክ መያዣዎችን መቀነስ 22

ከፎም የጸዳች አሌክሳንድሪያ

የበዓል ቆሻሻን መቀነስ 23

ለመቀነስ፣ ዳግም ለመጠቀም እና መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች 24

እኛን እንዴት ያገኛሉ 25

ተገናኝተው ይቆዩ 25





# ስለ T&ES የኃብት መልሶ ማግኛ ክፍል

ለመኖር ምቹ፣ አረንጓዴ እና የበለጸገ ማህበረሰብን ለመጠበቅ በTransportation & Environmental Services (T&ES) መምሪያ ውስጥ ያለው የአሌክሳንድሪያ ከተማ የኃብት መልሶ ማግኛ ክፍል በእያንዳንዱ ቀን ይሰራል።

የቡድን አባላት የመንገድ መጥረጊያዎችን ሲጠርጉ ወይም በፀደይ ወቅት ብስባሽ ሲሰበስቡ እና በመኸር ወቅት ቅጠሎችን ሲያጸዱ ይመለከታሉ። የኃብት መልሶ ማግኛ ሰራተኞች ከቤትዎ የተጣሉ ነገሮችን ሲሰበስቡ፣ መልሰው ጥቅም ላይ ሲያውሉ እና የጓሮ ቆሻሻን ሲሰበስቡ እና የጋራ ቦታዎች ጽዱ ለማድረግ የቆሻሻ መሰብሰቢያ እቃዎችን በመድፋት፣ ቆሻሻን በመሰብሰብ እና ህገወጥ ቆሻሻ መጣልን ሲከላከሉ ሊገኙ ይችላሉ።

ስለኃብት መልሶ ማግኛ ክፍል እና [alexandriava.gov/ResourceRecovery](alexandriava.gov/ResourceRecovery) ላይ በመጎብኘት ከተማው እንዴት በዘላዊነት ኃብቶችን መልሶ ማግኘት እንደሚችል እንደሚረዱ የበለጠ ይወቁ።



**Flavio Goncalves**

*የኃብት መልሶ ማግኛ ክፍል ዋና ኃላፊ፣*

## ከክፍል ዋና ኃላፊው የተላለፈ መልእክት

የኃብት መልሶ ማግኛ ክፍል መመሪያ የመጨረሻ እትምን ለመገምገም ስለወሰዳችሁት ጊዜ እናመሰግናለን! ቡድናችን ለአሌክሳንድሪያ ከተማ ዓመቱን በሙሉ አስፈላጊ የሆኑ አገልግሎቶችን ይህም የደረቅ ቆሻሻ እና የመልሶ አገልግሎት ላይ የማዋል አሰባሰብ፣ የጎዳና ጽዳት እና ሌሎች የዘላቂነት ፕሮግራሞችን ጨምሮ ለማቅረብ ቁርጠኛ ነው። ከእነዚህ አገልግሎቶች እንዴት ጥቅም ሊያገኙ እንደሚችሉ አጠቃላ እይታን ለማጋራት በጉጉት እየጠበቅን እንገኛለን።

በዚህ መመሪያ ውስጥ የተዘረዘሩ ምርጥ ልምምዶችን ለመከተል ያደረጓቸውን ቀጣይነት ያለው ድጋፍ እና መሰጠት ከልብ እናደንቃለን። ጥረትዎ ንጹህ እና የበለጠ ዘላቂ አሌክሳንድሪያን የማየት አስተዋጽኦ ብቻ ሳይሆን በጊዜው የሆነ እና ውጤታማ የአገልግሎት መዳረሻን ለማረጋገጥ ደከመኝ ሳይሉ ለሰሩ የእና የኃብት ማልሶ የማግኘት ሰራተኞች እና ስራ ተቋራጮች ደህንነት ቅድሚያ እንዲያገኝ ያግዛል።

በጋራ በመሆን የከተማውን አካባቢያዊ ግቦች ለማሟላት በመስራት ጠንካራ፣ ንጹህ ማህበረሰብን ጎን ለጎን እንገነባለን።

በእነዚህ ስኬቶች ላይ መገንባታችንን እንቀጥል። በጋራ በመስራት፣ ለነገ ከዚህም የበለጠ ዘላቂ የሆነ አሌክሳንድሪያን በመፍጠር ትርጉም ያለው ልዩነት ማድረግ እንችላለን።

# ሳምንታዊ የአሰባሰብ አገልግሎቶች




## ብቁ የሆነው ማን ነው?

በተነጠሉ የነጠላ ቤተሰብ ቤቶች፣ ዱፕሌክሶች እና አራት ወይም ከዚያ በታች ክፍሎች ያሏቸው አንዳንድ የከተማ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩ የአሌክሳንድሪያ ከተማ ነዋሪዎች የዚህ በክፍያ ላይ የተመሰረተ የሚያስፈልግ የአገልግሎት ተጠቃሚዎች ናቸው። የንግድ ንብረቶች እና የኮንዶሚኒየም ኮምፕሌክሶች የሚጠየቁ ተጠቃሚዎች አይደሉም፣ ነገር ግን በነጻ የከተማው ውሳኔ ሊሳተፉ ይችላሉ።

## የእኔን ውጋጅ መሰብሰብ እንዴት አዘጋጃለሁ?


- ተመልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉት በሰማያዊ ከተማ የቀረበ የመልሶ መጠቀሚያ መያዣ ውስጥ ሳይታሰሩ መቀመጥ አለባቸው ***የፕላስቲክ መያዣዎች አይቻልም***

- የጓሮ ቆሻሻ በደንበኛ የቀረበ የዳግም አጠቃቀም የማይተጣጠፍ መያዣ ወይም የወረቀት የጓሮ ቆሻሻ መያዣ (በግሮሰሪ እና በሃርድዌር መደብሮች ሽያጭ ይገኛል)

- ቆሻሻ በከተማው በቀረበ መያዣ ውስጥ መያዥ እና መቀመጥ አለበት።

## ቆሻሻ ለመሰብሰብ የት አስቀምጣለሁ?

ለአብዛኞቹ ነዋሪዎች፣ መሰብሰብ የሚከናወነው በቤትዎ ፊት ባለው የጋራ ቦታ ሲሆን አንዳንድ ነዋሪዎች ግን የመንገድ ላይ አሰባሰብ ያገኛሉ። የቆሻሻዎ አሰባሰብ የት እንደሚደረግ እርግጠኛ ካልሆኑ፣ **Alex311** ላይ ይገናኙ። የመሰብሰብያ መያዣዎች በእርስዎ የአገልግሎት ቀን ላይ እስከ 7 p.m. ከጋራ መጠቀሚያ ቦታ ይወገዳሉ።




*ሳምንታዊ የአሰባሰብ ካርታ*

## ቆሻሻዬን እንዲሰበሰብ መቼ አወጣለሁ?

እያንዳንዱ ደንበኛ በከተማው ውስጥ ባሉበት ቦታ ላይ በመመስረት የስብስብ ቀን ላይ ይመደባል። ለእርስዎ የመሰብሰቢያ ቀን በAlex311 ላይ ያግኙ ወይም alexandriava.gov/RefuseCollection ላይ ይጎብኙ። ቆሻሻ፣ ቆሻሻን መልሶ የመጠቀም እና የጓሮ ውጋጅ አስቀድሞ ባለው ቀን ከ5 p.m. በኋላ እና ከ6 p.m. በፊት መነሳት አለበት።

የሚሰበስቡት ሰራተኞች በበጋ በ6 a.m. በሚሰበሰብበት ጊዜ ካልሆነ በቀር ከሰኞ እስከ አርብ ከ7 a.m.-5 p.m. ባሉት ሰዓታት ውስጥ ያከናውናሉ። መሰብሰብ ዓመት በአል ሲሆን ወይም ያልታሰቡ ሁኔታዎች ሲከሰቱ በሚኖሩ ሳምንታት ውስጥ በአንድ ቀን ከፍ ወይም ዝቅ ሊል ይችላል።

## እርስዎ የእኔ መሰብሰብ አልፎዎታል!

ኃብቶችን መልሶ ለማግኘት፣ ደህንነቱ የተጠበቀ አሰባሰብን ለማረጋገጥ እና አካባቢውን ጽዱ እና ንጹህ ለማድረግ የእርስዎ የቆሻሻ አሰባሰብ የእቃ ዝግጅት ወሳኝ ነው።

የእርስዎ እቃ በቀኑ መጨረሻ ካልተሰበሰበ፣ ከተማው ለምን እንዳልሰበሰበ የሚያስረዳ መለያን ይፈትሹ።

## የተለመዱ ችግሮች የሚያካትቱት:-

- የመሰብሰቢያ መያዣ፣ ከረጢት ወይም እቃው በጣም ከባድ ነው።
- እቃው እንደ ምንጣፍ ወይም እንጨት ከ4 ጫማ በላይ ነው።
- እንደ ግንባታ ቁርጥራጮች፣ ቆሻሻ፣ ጡብ እና ድንጋዮች ያሉ ተቀባይነት የሌላቸው ነገሮችን ከያዘ (ነዋሪዎች እነዚህን እቃዎች ለማስወገድ የግል ማስወገጃ ጋር መደወል አለባቸው)።
- እንደ ቤንዚን ያሉ አደገኛ እና ችግር ሊፈጥሩ የሚችሉ ፈሳሾች እንዲሁም በቆርቆሮ ውስጥ ያለ ያልደረቀ ቀለም።
- ቆሻሻ ከመልሶ አገልግሎት ላይ ማዋያ ጋር ሲደባለቅ

**መለያ የለም?** በAlex311 ላይ **"ያመለጠ ስብስብ" ቲኬትን ያስገቡ።**




## የመልሶ መጠቀም የጋሪ መጠኖች

የቆሻሻ ጋሪ በአንድ መጠን (65 ጋሎን) ቢመጣም፣ የመልሶ አገልግሎት ላይ የማዋያ ጋሪዎች ከላይ በምስሉ እንደሚታዩት በሶስት የተለያዩ መጠኖች ይመጣሉ።

## ቆሻሻዬን ለማውጣት ወይም የመልሶ አገልግሎት ላይ ማዋል ላይ እገዛ እፈልጋለሁ።

ወደ መንገድ ጠርዙ ወይም ወደ መንገዱ በአካል ቆሻሻዎን ለማውጣት ወይም የመልሶ አገልግሎት ላይ ማዋል ካልቻሉ፣ ማመቻቸት ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ፈቃድ ካገኙ፣ ሰራተኞች ለእርስዎ በሚስማማ ቦታ ከቤትዎ ውጪ የተቀመጠ ማስቀመጫ ቆሻሻ እና የመልሶ መጠቀሚያ ግብዓትን ያስወግዳል።

ማመልከቻ ለመቀበል **Alex311**ላይ ይደውሉ። ይህ አገልግሎት ለጓሮ ውጋጅ አይቀርብም።

# መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል

የመልሶ መጠቀሚያ ግብዓት ገበያዎች ያለማቋረጥ ይቀያየራሉ። እነዚህ ገበያዎች ሲቀያየሩ፣ የመለያ ቴክኖሎጂዎች፣ የፓኬጂንግ ንድፎች እና የግብዓቶቹ መልሶ የመጠቀም ደረጃም ይቀየራል።

ከተማው እነዚህን ለውጦች ከግምት ውስጥ ለማስገባት የመልሶ መጠቀሚያ ግብዓት ፕሮግራምን በመደበኛነት ይገመግማል እንዲሁም ያስተካክላል እና ወደ መልሶ መጠቀሚያ ግብዓት የቱ እንደሚሆን እና እንደማይሆን ግንዛቤ እየሰጠዎት ይቆያል።

## *በሰማያዊ መያዣ ውስጥ የማይደረጉ ተመልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉ እቃዎችስ?*

የከተማ መልሶ የመጠቀም አሰባሰብ አገልግሎትን የሚያገኙ ነዋሪዎች ከፍተኛ መጠን ላላቸው የብረት እቃዎች የማንሳት መርኃግብር ሊያወጡ ይችላሉ። የቤት ውስጥ የብረት መገልገያ መሳሪያዎች እና የውጪ ግሪሎች፣ የአካል ብቃት መሳሪያ እና በሰንሰለት የታሰረ አጥርን የመሳሰሉ ትላልቅ የብረት እቃዎች በተጠየቀው መሰረት መልሶ መጠቀም ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ (ክፍያዎች ይተገበራሉ)።

የአገልግሎት ጥያቄን ለማቅረብ **Alex311** ላይ ያነጋግሩ።

## *በሰማያዊ መያዣው ውስጥ ምን መልሼ ጥቅም ላይ ላውል እችላለሁ?*





✔ **ወረቀት እና ካርቶን**
**ባዶ ያድርጉት እና ያጣጥፉት**



✔ **የፕላስቲክ መያዣዎች**
**ባዶ ያድርጉት እና ይጠቡት**
**መለያዎች ይፈቀዳል**



✔ **የብረት መያዣዎች**
**ባዶ ያድርጉ እና ይጠቡ**
**መለያዎች ይፈቀዳል**




✘ **መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል አይቻልም!**



**ባትሪዎች እና ኤሌክትሮኒክስ አይቻልም**
**ልብስ ወይም ጨርቃጨርቅ አይቻልም**
**ታንግለርሶች (ገመዶች እና ሽቦዎች) አይቻልም**
**መምጠጫዎች/ዕቃዎች አይቻልም**
**ስታይሮፎም አይቻልም**
**መስታወት አይቻልም**
**የፕላስቲክ ከረጢት አይቻልም**
**ትላልቅ እቃዎች አይቻልም**
**የተቆራረጠ ወረቀት አይቻልም**
**የቤት እንስሳት ውጋጅ/ዳይፐሮች አይቻልም**
**የሕክምና ውጋጅ/ስለታማ ነገሮች አይቻልም**
**የምግብ ትርፍራፊ አይቻልም**

# የመልሶ መጠቀሚያ መመሪያዎች

1. እቃዎቹ ንጹህ፣ ባዶ እና ደረቅ መሆን አለባቸው። አስፈላጊ ከሆነ ውሻ ያፍስሱበት። የምግብ ትርፍራፊ አይቻልም።
2. ቆሻሻ መያዣዎቹን ባዶ ካደረጉ በኋላ መልሰው ይክደኑ።
3. ከ3X3 ኢንች በታች የሆኑ እቃዎች በመልሶ መጠቀሚያ መሳሪያ ሾልከው ያልፋሉ። መገልገያዎች ወይም መምጠጫዎች አይቻልም።
4. ካርቶኖቹን ባዶ ያድርጉ እና ያጣጥፉ። ከካርቶኖቹ የአየር ትራሶች፣ ስታይሮፎም ወይም የፕላስቲክ መጠቅለያ ያስወግዱ።
5. የፕላስቲክ ቁጥሮች (ከቁጥር 1 እስከ 7) የመልሶ አጠቃቀም ደረጃን አይወስንም። በ#1 እና #2 ፕላስቲኮች የተሰሩ አንገት ያላቸው የማይተጣጠፍ የፕላስቲክ መያዣዎች በክልሉ ውስጥ በሰፊው መልሰው ጥቅም ላይ ይውላሉ።
6. የፕላስቲክ ክዳኖች፣ የማውጫ መያዣዎች እና የፕላስቲክ የምግብ መያዣዎች**ምንም የምግብ ትራፊ ከሌለ**እና እቃው **በሚገባ ከታጠበብቻ መልሰው ጥቅም ላይ ማዋል ይችላሉ።**
7. ለመስመር ላይ የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ መሳሪያዎች እና በጣም የቅርብ ጊዜ የሆነ የአዎ/አይ ዝርዝር [alexandriava.gov/Recycling](alexandriava.gov/Recycling) ላይ ይጎብኙ።

## በትክክል መልሰው ጥቅም ላይ ያውሉ
## አሌክሳንድሪያ፦



**የፕላስቲክ ከረጢቶች አይፈቀዱም**

# መልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉ ነገሮችን
# አይክተቱ



# በመልሶ ጥቅም ላይ ማዋል የፕላስቲክ መያዣዎች አይቻሉም!

የፕላስቲክ መያዣዎች፣ መጠቅለያዎች እና የማናቸውም ቀለም፣ መጠን ወይም ቅርጽ ፊልሞች በከተማው የመልሶ መጠቀሚያ ማጠራቀሚያዎች ተቀባይነት የላቸውም። እነዚህ እቃዎች የመልሶ አጠቃቀም መሳሪያን በመድፈን በሰራተኞች ላይ የደህንነት አደጋዎችን እንዲሁም የኦፕሬሽን ችግሮችን ያስከትላሉ።

የመልሶ ጥቅም ላይ የማዋል ፋሲሊቲዎች በፕላስቲክ ቆሻሻ ውስጥ ከተያዙ ወይም መጠቅለያዎች እና የትኞቹም የፊልም አይነትን ካካተቱ ብዙ ጊዜ ውድቅ ይደረጋሉ። መያዣዎች እና መጠቅለያዎች ከቀረቡ በተጨማሪም ከተማው ቅጣት ይከፍላል።

የፕላስቲክ መያዣዎች ብዙ ጊዜ በከተማው የመልሶ መጠቀም ፍሰት ውስጥ ቁጥር አንድ በካይ ነው፤ እባክዎ የመልሶ መጠቀሚያዎችዎን ለቀቅ በማድረግ ብክለትን እንዲቀንስ ያግዙ።

## *የፕላስቲክ መያዣ መጣያ*

የፕላስቲክ ከረጢቶች፣ መጠቅለያዎች እና ፊልሞች ንጹህ ከሆኑ፣ ባዶ ከሆኑ እና በተሳታፊ የግሮሰሪ መደብሮች እና መሸጫዎች ከወረዱ መልሰው ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ።



**የፕላስቲክ ከረጢቶችን ወደ ሻጮች ይመልሱ።**

የቅርብ ሻጭ ያግኙ፦
plasticfilmrecycling.org

# የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋል መጣያ ማዕከላት

አሁኑኑ መልሰው ጥቅም ላይ ለማዋል ይፈልጋሉ? ከተማው ሁሉም የከተማው ነዋሪዎች እና አነስተኛ የንግድ ስራዎች እንዲጠቀሙባቸው አራት የጋራ የመጣያ ማዕከላትን አቅርቧል።

4251 Eisenhower Avenue

3224 Colvin Street

Jones Point Park (በSouth Royal Street የግራ መጨረሻ ወደ ደቡብ የሚሄደው)

South Whiting Street (በSouth Whiting Street መጨረሻ ላይ፣ ከTower Court ጋር ይገናኛል)

**በቀን ለ24 ሰዓታት፣ በሳምንት ለሰባት ቀናት**

**ነፃ**


[alexandriava.gov/go/1792](alexandriava.gov/go/1792)

## ተቀባይነት ያላቸው እቃዎች፦

- ድብልቅ መያዣዎች (የአሉሚኒየም ጣሳዎች፣ የብረት ጣሳዎች፣ የፕላስቲክ ጠርሙሶች እና ጆጎች)
- ድብልቅ ወረቀት
- ባዶ እና የተጣጠፈ ካርቶን (ስታይሮፎም እና የፕላስቲክ መጠቅለያን ያስወግዱ)

## የተከለከሉ ነገሮች፦

- መስታወት (ዳግም ጥቅም ላይ በሚውሉ ማዕከላት በጋራ ያሉትን የወይን ጠጅ ማጠራቀሚያዎች ይጠቀሙ)
- ስታይሮፎም ወይም የመጠቅለያ ለውዞች
- ሸክላ ድስቶች እና መጥበሻዎች
- የፕላስቲክ መያዣዎች፣ መጠቅለያዎች ወይም ፊልሞች
- ቆሻሻ፣ ፈርኒቸር፣ የተከማቸ ቆሻሻ፣ የግንባታ ውጋጅ ወይም የጓሮ ቆሻሻ(ህገወጥ ቆሻሻ መጣል አይቻልም)




## ሕገወጥ ቆሻሻ መጣልን እንድንፋለም ያግዙን




ሕገወጥ ቆሻሻ መጣል ደህንነቱ የተጠበቀ እና በትክክል የተቀመጡ የመልሶ መጠቀሚያ ማዕከላት ኦፕሬሽንን ይገድባሉ እና የአካባቢ እና ሕዝባዊ የጤና ስጋቶችን ይደቅናል።

ማህበረሰብ ንጹህ፣ ጤናማ እና ደህንነቱ የተጠበቀ አድርጎ ለማቆየት የአሌክሳንድሪያ ከተማ ይህንን ሕዝባዊ ሸክም ለመፋለም በቁርጠኝነት ይሰራል።

በሒደቱ ላይ ያዩት ማናቸውም ጥሰቶችን አሉ? በከተማው ውስጥ ህገወጥ ቆሻሻ መጣልን **Alex311**ን በመገናኘት ሪፖርት ያድርጉ።






# መስታወት


## በሰማያዊ የመልሶ ጥቅም ላይ የማዋያ ማጠራቀሚያዎች ውስጥ ጠርሙስ መጣል አይቻልም!

መስታወት በመንገድ ጠርዝ የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ ፕሮግራም ተቀባይነት የለውም።

### ነዋሪዎች ሁለት አማራጮች አሏቸው፦

1. በክልሉ ሁሉ በከተማው የዳግም ጥቅም ላይ ማዋያ ማዕከላት እና ተጨማሪ ቦታዎች ላይ በሚገኙ የወይን ጠጅ የመስታወት ብቻ የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ ማጠራቀሚያዎች መስታወት ይጣሉ።
2. መስታወት በመንገድ ጠርዝ ባሉ የቆሻሻ ጋሪዎች ውስጥ ያድርጉ።

በወይን ጠጅ ማጠራቀሚያዎች ላይ የተጣለ መስታወት ወደ አዲስ የመስታወት ተርሙሶች፣ የፋይበርግላስ መሸፈኛ እና በአካባቢ የስራ ፕሮጀክቶች ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ እቃዎች መልሰው ጥቅም ላይ ይውላሉ።




## አዎ!



- ባዶ ያድርጉ እና በውሃ ያለቅልቁት
- መለያዎች - ይፈቀዳል
- ሁሉም የመስታወት ቀለሞች - ይፈቀዳል
- የጠርሙስ መክደኛዎች እና ሊዶች - ይፈቀዳል

## አይደለም!



**መስታወት አይክተቱ**ወይም በፕላስቲክ ወይም የፕላስቲክ ማሰሪያዎች አይጠቅልሉ



የፕላስቲክ መያዣዎች አይቻልም (ወደ ሻጩ ይመልሱ)



ምንም አምፖሎች ወይም የሚበሩ ነገሮች አይቻልም (በ3224 Colvin St. የቤት ውስጥ አደገኛ የውጋጅ ማዕከልን ይጠቀሙ)



ሴራሚክስ፣ ፖርስሌን፣ ብርጭቆዎች፣ መስኮቶች፣ ፋይሬክስ ወይም የመስታወት ሉሆች አይቻልም



ምግብ ወይም ፈሳሽ አይቻልም (ባዶ ያድርጉ እና ያለቅልቁ)

- 4251 Eisenhower Avenue
- 3224 Colvin Street
- Jones Point Park (በSouth Royal Street የግራ መጨረሻ ወደ ደቡብ የሚሄደው)
- South Whiting Street (በSouth Whiting Street መጨረሻ ላይ፣ ከTower Court ጋር ይገናኛል)
- በNorthern Virginia ያሉ ተጨማሪ መገኛዎች በ alexandriava.gov/go/2771 ላይ ሊገኙ ይችላሉ

በቀን ለ24 ሰዓታት፣ በሳምንት ለሰባት ቀናት

ነፃ

alexandriava.gov/go/2771




## ለእርስዎ ልዩ ክንውን የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ መያዣዎች ይፈልጋሉ?

የአሌክሳንድሪያ ከተማ የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ ፕሮግራም በአሌክሳንድሪያ ከተማ ውስጥ ላሉ ክንውኖች መበደር የሚቻልባቸው ClearStream የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ መያዣዎች አለው።


የሙሉ መያዣው የብድር ስምምነትን ለመገምገም እና ከClearStream መያዣዎች ጋር ያለ ክንውን ላይ እቅድ የማውጣት ሙሉ ደረጃዎችን ለማግኘት፣ alexandriava.gov/go/2723 ላይ ይጎብኙ




# በልዩ ክንውኖች ላይ መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል

በእርስዎ ክንውን ላይ የቆሻሻ መጠንን ለመቀነስ መልሶ ጥቅም መዋል በጣም ቀላል እና ርካሽ ከሆኑ መንገዶች አንዱ ነው። መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል በአራት ቀላል እርምጃዎች ሊደረግ ይችላል፦

1. ***በእርስዎ የክንውን ቦታ መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል እና በተለይ ደግሞ ለትላልቅ ክንውኖች አስተባባሪን ለማቋቋም ይወስኑ።***
2. ***የስብስብ ስርዓትን ያቅዱ እንዲሁም ያዋቅሩ።***
    - ምን አይነት የቆሻሻ እና የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ መያዣዎችን ይጠቀማሉ?
    - ምን ያህል የቆሻሻ እና የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ መያዣዎችን ይጠቀማሉ? (የመጀመሪያው መመሪያ ለእያንዳንዱ የቆሻሻ ጣሳ አንድ የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ መያዣ።)
    - የቆሻሻ እና የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ መያዣዎች የት ይገኛሉ? የቆሻሻ እና የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ መያዣዎች በሚገባ በሚታዩ እና በቀላሉ ተደራሽ በሆኑ መገኛዎች ውስጥ አንዱ ከሌላው ጎን መሆን አለባቸው።
    - የቆሻሻ እና የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ መያዣዎችን ባዶ ለማድረግ ማን ኃላፊነቱን ይወስዳል? በክንውኑ መጨረሻ ላይ ቆሻሻውን ማን ያስወግዳል እንዲሁም መልሶ ጥቅም ላይ ያውላል? (የቆሻሻ መኪና፣ ግለሰብ ወዘተ. ለአነስተኛ ክንውኖች፣ የከተማው የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋል የመጣያ ቦታዎ ይገኛሉ።)
3. ***መሰረታዊ የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ ትምህርትን ያስተዋውቁ እንዲሁም ያቅርቡ።***
    - መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚኖር በክንውኑ መጀመሪያ እና በክንውኑ ውስጥ ሁሉ ያስተዋውቁ።
    - በእርስዎ ክንውን ላይ ምን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚቻል የሚያስረዱ ምልክቶችን ያቀርቡ።
    - የቆሻሻ እና የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ መያዣዎች በአግባቡ መለያ እንደተሰጣቸው ያረጋግጡ።
4. ***ለማንኛውም ብክለት (በመልሶ ጥቅም ላይ የማዋያ መያዣ ውስጥ ያለ ቆሻሻ ወይም በተቃራኒው) የቆሻሻ እና የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋል መያዣዎችን ይቆጣጠሩ።***
    - በተለይ ለትላልቅ ክንውኖች በጎ ፈቃደኞች ምን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚቻል እና ምን እንደማይቻል እንዲሁም መልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉት የት እንደሚሄዱ ለክንውን ተሳታፊዎች ያስታውሱ።






# የጋራ ቦታ መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል

**የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ መያዣዎች እንደ lower King Street እና Mount Vernon Avenue እና City parks ባሉ ታዋቂ የእግረኛ አካባቢዎች ውስጥ ይገኛሉ።**

## በጋራ መያዣው ውስጥ መልሼ ጥቅም ላይ የማውለው ምንድን ነው?

✔ ወረቀት እና ካርቶን
ባዶ ያድርጉት እና ይዘረጋጉት

✔ የፕላስቲክ መያዣዎች
መለያዎች ይፈቀዳሉ

✔ የብረት መያዣዎች
መለያዎች ይፈቀዳሉ

### ተቀባይነት ያላቸው እቃዎች፦

- የአሉሚኒየም ጣሳዎች
- የፕላስቲክ ጠርሙሶች
- ድብልቅ ወረቀት (ትላልቅ ካርቶን አይቻልም)

✘ መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል አይቻልም!

### የተከለከሉ እቃዎች፦

- መስታወት አይቻልም (በመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ ማዕከላት በጋራ የሚገኙ የሐምራዊ ቆሻሻ መጣያዎችን ይጠቀሙ)
- የቤት እንስሳት ቆሻሻ አይቻልም
- ሸክላ ድስቶች እና መጥበሻዎች
- የፕላስቲክ መያዣዎች፣ መጠቅለያዎች ወይም ፊልሞች
- ትላልቅ የቆሻሻ ክምር አይቻልም
- የምግብ መያዣዎች አይቻሉም (ለምሳሌ፦ የሚወሰድባቸው መያዣዎች፣ ኩባያዎች ወይም ሳህኖች)



## በሰማያዊው ውስጥ መጸዳዳት አይቻልም

የጋራ ቦታዎች ንጹህ ሆነው እንዲቆዩ የቤት እንስሳት ቆሻሻን ማንሳት እና በመሰብሰቢያ ውስጥ መያዝ አስፈላጊ ነው። የቤት እንስሳት ውጋጅ በቆሻሻ ብቻ መያዣ እቃዎች መደረግ አለባቸው፤ ሰማያዊ የመልሶ ጥቅም ላይ የማዋያ መያዣዎች ከብክለት ነጻ መሆናቸውን ያረጋግጡ!

የቤት እንስሳት ውጋጅን በመልሶ ጥቅም ላይ የማዋያ መያዣ ውስጥ ማስቀመጥ ሁሉም መልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉ ነገሮችን በማበላሸት ከተማው ሁሉንም የመያዣ ይዘቶች እንደ ቆሻሻ እንዲለይ ያደርገዋል።

ጎዳናዎች፣ የእግረኛ መንገዶች እና ፓርኮች ንጹህ እንዲሁም የጋራ መልሶ የመጠቀሚያ መያዣዎች ከብክለት ነጻ አድርገው ለማቆየት እያገዙ ስለሆነ እናመሰግናለን!

# የጓሮ ቆሻሻ




ከተማው ሳር፣ ቅጠሎች፣ አረም እጽዋት፣ ቅርንጫፎች እና የደረቁ ተክሎችን እንደ ኦርጋኒክ ማዳበሪያ እና የበሰበሱ የተክል አካላት ማድረግ ይችላል። የጓሮ ቆሻሻ ተብሎ የሚጠራው ይህ ኃብት ከቤት ቆሻሻ ተነጥሎ ይሰበሰባል።

የጓሮ ቆሻሻን ጠንካራ እና እንደገና ጥቅም ላይ በሚውሉ መያዣዎች ወይም የወረቀት የጓሮ ቆሻሻ መያዣዎች (በግሮሰሪ እና የሃርድዌር መደብሮች ለመግዛት ይገኛል) ያስቀምጡ እና ወደ እርስዎ የቆሻሻ መያዣ ጎን ያስቀምጡ። ከተማው የጓሮ ቆሻሻ መያዣዎችን አያቀርብም፣ አይዝም ወይም አይተካም። መሰብሰብ ልክ እንደ ቆሻሻ በተመሳሳይ ቀን ይከናወናል።

- ሳር
- አረም እጽዋት እና ቅርንጫፎች
- የደረቁ ተክሎች
- ቅጠሎች

- ድንጋዮች፣ አፈር
- ጉቶዎች፣ ሳር የበቀለበት መሬት
- የቤት እንስሳት ቆሻሻ



## የክሪስማስ ዛፎች

በከተማ መሰብሰብ የሚያገኙ ነዋሪዎች በጃንዋሪ ወር መደበኛ የተከለከሉ ቀናት በመንገድ ጠርዝ ላይ የተፈጥሮ ክሪስማስ ዛፎችን ሊያስቀምጡ ይችላሉ። ዛፎች ወደ ጥድ ብስባሽ ይቆራረጣሉ። መቆሚያዎች፣ ቆርቆሮዎች፣ ማስጌጫዎች እና መብራቶች መወገድ አለባቸው።



## የጸደይ ቅጠር እና የእንጨት ብስባሽ

በጸደይ እና በበጋ ወቅት ለተወሰነ ጊዜ፣ ነጻ ብስባሽ መጀመሪያ ለመጣ፣ መጀመሪያ ለተገለገለ በሚለው መሰረት ከከተማው የብስባሽ ጣቢያ (4251 Eisenhower Avenue) ላይ ይገኛል።

በጸደይ እና በቅድመ በጋ ወራት ወቅት የብስባሽ አቅርቦት መርኃግብር ለማስያዝ እርስዎ ወደ **Alex311** ሊደውሉ ወይም ሊጎበኙ ይችላሉ። አቅርቦት ለእያንዳንዱ ግማሽ ጭነት $65 እንዲሁም ለሙሉ ጭነት $130 ነው። አቅርቦቶች ከሰኞ እስከ አርብ መርኃግብር ተይዞላቸዋል እና ቅዳሜና እሁድ ወይም በዓላት ላይ መርኃግብር ሊያዝባቸው አይችልም።

## ከፍተኛ ክምችት ያለው የጓሮ ቆሻሻ - በጥያቄ

በቆሻሻ መያዣ ውስጥ ለማስቀመጥ በጣም ትልቅ ወይም ከባድ የሆኑ አረም እጽዋት፣ ቅርንጫፎች እና እንጨቶች ጥያቄ ሲቀርብ ከመንገድ ዳር ሊሰበሰቡ ይችላሉ። ሰራተኞች እስከ ሁለት ድረስ በመንገድ ዳር ጠርዝ የወደቁ ዛፎችን(ገደቦች ይተገበራሉ፣ ከታች ያለውን ይመልከቱ) ይሰበስባሉ።

የመሰብሰብ ቀን**ላይ መርኃግብር ለማስያዝ** Alex311 ይጠቀሙ።

## ዝግጅት

- መሰብሰብ በዲያሜትር ከ18 ኢንች በታች ለሆኑ እና ርዝመታቸው ከ10 ጫማ ለማይበልጡ ግንዶች እና ቅርንጫፎች ብቻ ይገኛል። የዛፍ ግንዶች አይቻሉም።
- አረም እጽዋትን በግቢ ወይም በመንገድ ውስጥ ሳይሆን በመንገድ ጠርዝ ያድርጉ። ትላልቅ እቃዎችን ከመንገድ ጠርዙ ትይዩ ያከማቹ።
- 25 ጫማ የሆነ ከላይ ያለው ጽዳት ያስፈልጋል (የኃይል መስመሮች እና የዛፍ ፍልጦችን ይጠንቀቁ)
- አረም እጽዋትን ከእንጨት ወይም የግንባታ ፍርስራሾች ጋር አይደባልቁ።
- አረም እጽዋትን የቆሙ ተሽከርካሪዎች ጋር አያስቀምጡ፤ 10 ጫማ ባዶ ቦታ ያስፈልጋል።
- አረም እጽዋትን እንደ ፖሎች፣ ልጥፎች፣ አጥሮች፣ ግንቦች ወይም ህንጻዎች ከመሳሰሉ ቋሚ ነገሮች ጋር አይቆልሉ።
- የእግረኛ መንገዶችን አይዝጉ።

የእርስዎን የጓሮ ቆሻሻ መያዣ ለመለየት“**የጓሮ ቆሻሻ ብቻ**”የሚለውን ለመጠየቅ**Alex311** ላይ ያነጋግሩ።

alexandriava.gov/YardWaste






# የቅጠል አሰባሰብ

አመታዊ የመንገድ ጠርዝ የቅጠል አሰባሰብ ፕሮግራም የከተማ መኖሪያ የክልከላ እና የዳግም ጥቅም ላይ ማዋያ አገልግሎቶችን ለሚያገኙ ነዋሪዎች በሙሉ የቀረበ አገልግሎት ነው። ከኦክቶበር መጨረሻ እስካ ጃንዋሪ፣ የከተማ ሰራተኞች የቅጠል ሰብሳቢ የቆሻሻ መኪኖችን ያንቀሳቅሳሉ እንዲሁም የወረቀት ቅጠል መያዣዎችን ይሰበስባሉ። አሌክሳንድሪያ በአምስት የመሰብሰቢያ ዞኖች የተከፈለ ሲሆን፣ እያንዳንዱ የተወሰነ የጅማሬ ቀን እና ሶስት የተናጠል ማለፊያዎች፣ የአየር ጸባይ ማሳለፊያ ወቅቶች ተቀምጠዋል።

በቤት አድራሻ ላይ በመመስረት የተመደቡ የቅጠር አሰባሰብ ቀናትን ለመመልከት ነዋሪዎች የመኖሪያ ቅጠል አሰባሰብ ተመልካች (በከተማው የቅጠል አሰባሰብ ድረገጽ ላይ ያለ መስተጋብራዊ ካርታ) መዳረሻ ማግኘት ይችላሉ።




*የማሰባሰብ ዞኖች ካርታ*

# የእርስዎን ቅጠሎች መልሶ ጥቅም ላይ የማዋያ ሶስት መንገዶች

የከተማ ቆሻሻ እና የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ የአሰባሰብ አገልግሎቶችን የሚቀበሉ ነዋሪዎች ቅጠሎችን በሶስት መንገዶች መልሰው ጥቅም ላይ ሊያውሉ ይችላሉ፦

## *1) ቅጠልን በአየር መሳቢያ መሰብሰብ*

በቅጠል ወቅት፣ ሰራተኞች በአየር መሳቢያ መጫኛ መኪና የፊት ጠርዝ ላይ የተሰበሰቡ ቅጠሎችን ይሰበስባሉ። የከተማ ሰራተኞች በእያንዳንዱ የሰፈር ዞን፣ የአየር ጸባይ ፈቃድ በኩል ሶስት ማለፊያዎችን ያደርጋሉ። በእያንዳንዱ ዞን ማሳለፍን ለማጠናቀቅ ሰራተኞች በርካታ ቀናት ይፈጅባቸዋል።

### እንዴት ማዘጋጀት ይቻላል

- ከእርስዎ የተመደበ የስብስብ ቀን (የዘመነ ሳምንታዊ መርኃግብር በከተማው ድረገጽ እና የማህበራዊ ሚዲያ ላይ ተለጥፏል) በፊት ቅጠሎችን በቀኑ ይሰብስቡ።
- ቅጠሎችን ወደ ጎዳናው ጠርዝ ፓይሎች ይሰብስቡ። ይህ ሰራተኞች በፍጥነት እና በቅልጥፍና እንዲሄዱ ያስችላቸዋል።
- ድንጋዮች፣ የእንስሳ መጸዳጃ፣ ቅርንጫፎችን እና ሌሎች ቁርጥራጮችን ያስወግዱ። እነዚህ ነገሮች መሳሪያ ላይ ጉዳት ሊያደርሱ እና ሰራተኞቻችንን ሊጎዱ ይችላሉ።
- ቅጠሎችን በጎርፍ ማፍሰሻዎች ወይም የውሃ ሜትር መሸፈኛዎች ፊት ለፊት ማስቀመጥ ያስወግዱ።
- የቆሙ መኪናዎችን ከቅጠል ፓይሎች ያንቀሳቅሱ።
- ቅጠሎችን ወደ ጎዳናዎች ወይም የአገልግሎት መንገዶች አይሰብስቡ። ጥቅልል ሶፍት ከጎዳናዎች ላይ አይሰበሰቡም

## 2) የቅጠል መያዣ መሰብሰቢያ

በቅጠል አሰባሰብ ወቅት፣ ከተማው የሚበሰብሱ የወረቀት ከረጢቶችን ለቅጠሎች መጀመሪያ የመጣ፣ መጀመሪያ ያገለገለ በሚለው መሰረት አቅርቦቶች እስከቆዩ ድረስ ያቀርባል። ከረጢቶቹ ነዋሪዎች እንዲወስዷቸው በበርካታ የከተማ ፋሲሊቲዎች ይገኛሉ እና ለንግድ መጠቀሚያ አይገኙም። ከረጢቶች በመሰብሰቢያ ቦታዎ (ቆሻሻዎን የሚያደርጉበት፣ መልሰው ጥቅም ላይ የሚያውሉበት እና የጓሮ ቆሻሻ የሚያወጡበት) በመደበኛ የቆሻሻ መሰብሰቢያ ቀን ይሰበሰባሉ።

### እንዴት ማዘጋጀት እንደሚቻል

- የወረቀት ከረጢቶቹን በእርስዎ የማሰባሰቢያ ቦታ በመደበኛ የቆሻሻ መሰብሰቢያ ቀን ላይ ያድርጉ። የወረቀት ከረጢቶችን ብቻ ይጠቀሙ። በፕላስቲክ መያዣዎች ውስጥ ያሉ ቅጠሎች ዳግም የሚሞሉ ተደርገው ይያዛሉ እና በReworld Energy-from-Waste ፕላንት ጋር እንደ ቆሻሻ ይጣላሉ።

- በከረጢቶቹ ውስጥ ከማስቀመጥ በፊት ቆሻሻ፣ ድንጋዮች፣ ቆሻሻ እንዲሁም ሌሎች ቁርጥራጮችን ያስወግዱ።



## 3) በቤት ያሉ የብስባሽ ቅጠሎች

በቤት ውስጥ ብስባሽን ማዘጋጀት የአካባቢን ተፈጥሯዊ የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ ሂደት ለመጠቀም ቀላሉ መንገድ ሲሆን በእርስዎ ጓሮ ዋጋ ያላቸው ተፈጥሯዊ ተጨማሪ ነገሮችን ይፈጥራል። የተቆረጡ ሳሮችን በዛው ስለመተው፣ የጓሮ ማዳበሪያ አዘገጃጀት እና [የከተማው የገበሬዎች ገበያ ማዳበሪያ አዘገጃጀት ጣቢያዎችን ለማወቅ](alexandriava.gov/ResourceRecovery) alexandriava.gov/ResourceRecovery ላይ ይጎብኙ።



# ኦርጋኒኮች

## አዲስ! የመንገድ ጠርዝ የምግብ ትርፍራፊ ማዳበሪያ ዝግጅት




የአሌክሳንድሪያ ከተማ ከእርስዎ የመንገድ ጠርዝ ላይ በመሆን ትልቅ የአካባቢ ተጽእኖን ለማድረግ አስደሳች አዲስ መንገድ ሲያሳውቅዎ ደስታ ይሰማዋል። በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የመንገድ ዳር የምግብ ትራፊ የማዳበሪያ አዘገጃጀት ፕሮግራምን ማስተዋወቅ፤ የከተማ ቆሻሻ እና የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ አገልግሎቶችን ከተቀበሉ፣ ምዝገባ ለማድረግ ብቁ ነዎት!

ከተማው አቅርቦቶችን ያቀርባል እና 75% የመሰብሰቢያ ወጪን ይሸፍናል፣ ይህም ፕሮግራሙን ጉልህ በሆነ ደረጃ በአካባቢዎ ካለው የተለመደ የመንገድ ጠርዝ የማዳበሪያ አዘገጃጀት የበለጠ ተመጣጣኝ ያደርገዋል። ከጁላይ 1፣ 2025 ጀምሮ የከተማ ቆሻሻ እና የመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ ስብስብ የሚያገኙ ነዋሪዎች **በወር $5** ወይም **በዓመት $55**ብቻ መርጠው መውጣት ይችላሉ።

ከቆሻሻ ክምር ይልቅ ያለውን በሙሉ ከአትክልት እና የፍራፍሬ ትርፍራፊ እስከ ስጋ እና አጥንት በንጥረ ነገር የበለፀገ ብስባሽ ማድረግ ይጀምሩ። የተጣሉ ነገሮችን ወዳዘጋጁት የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ይጣሉ!

ስለ እዚህ አገልግሎት የበለጠ ለማወቅ፣ እባክዎን በሚከተለው የእኛን ድረገጽ ይጎብኙ፦ alexandriava.gov/go/4289

የመሰብሰቢያ ቀናት በስራ ተቋራጭ ይወሰናል እና በደንበኛ ፖርታል በኩል ከምዝገባ በኋላ ሊገኝ ይችላል።

$5 በወር ወይም $55 በዓመት

alexandriava.gov/go/4289

### *እንደ ፕሮግራሙ ክፍል፣ ተሳታፊዎች የሚቀበሉት...*



ሳምንታዊ የመንገድ ዳር መሰብሰቢያ



ባለ7 ጋሎን የቆሻሻ መያዣ እና 40 BPI ወደ ብስባሽነት የሚቀየሩ ከረጢቶች ጋር ያለ የማስጀመሪያ ስብስብ እቃ




በየዓመቱ የማሟያ ብስባሽ ከረጢት

### *በመንገድ ጠርዝ ብስባሽ ላደርገው የምችለው ምንድን ነው?*

#### አዎ

- በBPI የተፈቀዱ ወደ ብስባሽነት የሚለወጡ እቃዎች
- የቡና አተላዎች እና ማጣሪያዎች
- የበሰለ እና የተጠበሰ ምግብ
- የወተት ተዋጽዖ
- የእንቁላል ቅርፊቶች
- የፍራፍሬ እና የአትክልት ትርፍራፊዎች
- ጥራጥሬዎች፣ እህሎች፣ ዳቦ እና ፓስታ
- አበባዎች እና በቤት የሚተከሉ የአትክልት ክርክሞች
- በብትን የሚመጣ ሻይ
- ስጋ እና አጥንቶች
- የቅባት ፍሬዎች እና ዘሮች
- የወረቀት ሶፍቶች እና ናፕኪኖች
- የተቀናበረ ምግብ
- የበሰበሰ ወይም የሻገተ ምግብ
- የባህር ምግብ

#### አይደለም

- የእንስሳት ውጋጅ
- ባትሪዎች
- ኬሚካሎች
- የሲጋራ ቁርጥራጮች
- ኮስሞቲክስ
- ዳይፐሮች
- በበሽታ የተጠቁ ተክሎች
- ኤሌክትሮኒክስ
- ተፈጥሯዊ ያልሆኑ እቃዎች
- የድመት መጸዳጃ
- መድኃኒት/የመድኃኒት ቆሻሻ
- ቀለም
- የአረም ማጥፊያዎች
- ፕላስቲኮች
- የምርት ተለጣፊዎች
- ጎማዎች
- የቆሸሹ ባንዴጆች
- መርዛማ ነገሮች
- በኬሚካል ጥቅም ላይ የዋሉ እንጨቶች
- የተጠቀለሉ ማሰሪያዎች
- ጥቅም ላይ የዋሉ ሶፍቶች

# በገበሬ ገበያዎች የምግብ ትርፍራፊ የማዳበሪያ ዝግጅት




የምግብ ትርፍራፊ በንጥረነገር በበለጸገ ተፈጥሯዊ ማዳበሪያ በነጻ ለመቀየር በቅዳሜና እሁድ የገበሬዎች ገበያ ላይ ሊጣል ይችላል። ስለ ማዳበሪያ ዝግጅት ያሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ እና የምግብ ትርፍራፊን እንዴት መቀነስ እንደሚቻል ምክር ለመስጠት ሰራተኞች በመስክ ላይ ናቸው።

## ብስባሽ አዎ


ለውዝ፣ ባቄላ፣ ዘሮች(ሼሎች/ቅርፊቶችን ጨምሮ)


የፍራፍሬ እና የአትክልት ትርፍራፊዎች


የቡና ዱቄት፣ ማጣሪያዎች፣ የሻይ ከረጢቶች (*መጠቅለያ ወይም በመጠቅለያ የተያዙ ምርቶች አይቻሉም*)


ዳቦ፣ ፓስታ፣ ሩዝ፣ እህሎች እና ጥራጥሬ


የእንቁላል ቅርፊት


አበባዎች

## ማዳበሪያ አይደለም


ዘይት


የፕላስቲክ ከረጢቶች


ስጋ፣ የባህር ምግብ እና አጥንቶች


የወተት ተዋጽዖ


ናፕኪኖች፣ ሶፍት


የቤት እንስሳት ቆሻሻ

## ቦታዎች

**Del Ray Farmers' Market**

Corner of East Oxford & Mount Vernon Avenues

ዘወትር ቅዳሜ፣ ከ8 a.m. - 12 p.m.

ዓመቱን ሙሉ ክፍት ነው

**Old Town Farmers' Market**

301 King Street, Market Square

ዘወትር ቅዳሜ፣ ከ8 a.m. - 12 p.m.

ዓመቱን ሙሉ ክፍት ነው

**Four Mile Run Farmers' Market**

4109 Mount Vernon Avenue

ዘወትር እሁድ፦ ከ9 a.m. - 1 p.m.

ዓመቱን ሙሉ ክፍት ነው

**West End Farmers' Market**

4800 Brenman Park Drive

ዘወትር እሁድ፣ ከ8.30 a.m. - 1 p.m.

ወቅታዊ ገበያ፦ ለቀናት ድረገጹን ይፈትሹ

**Old Town North Farmers Market**

901 North Royal Street

ዘወትር እሁድ፦ ከ10 a.m. - 2 p.m.

ዓመቱን ሙሉ ክፍት ነው

**Southern Towers Farmers Market**

4901 Seminary Rd

ዘወትር ቅዳሜ፦ ከ10 a.m. - 2 p.m.

ዓመቱን ሙሉ ክፍት ነው



## ምግብ ይቆጥቡ

### *40% የሚሆነው ጠቅላላ ምግብ በአሜሪካ ውስጥ ይባክናል።*

ከመጀመሩ በፊት የምግብ ብክነትን ማስቆም እና ምግብ መርዳት ማዳበሪያ ከማዘጋጀት በፊት ያሉ ምርጥ ተሞክሮዎች ናቸው። ስለ ምግብ ብክነት መከላከል ይወቁ፣ ምግብ የት መለገስ እንደሚቻል ማውጫ ያግኙ እና alexandriava.gov/FoodWaste ላይ በመጎብኘት ተጨማሪ ጥቅማጥቅሞችን ያግኙ።

# የቆሻሻ አገልግሎቶች

መልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉትን፣ የምግብ ትራፊ እና የጓሮ ቆሻሻን ከለዩ በኋላ፣ የሚቀረው የእርስዎ የቤት ቆሻሻ ነው። የአሌክሳንድሪያ ከተማ በየሳምንቱ በግምት ከ20,200 ደንበኞች ቆሻሻ ይሰበስባል። የምንሰበስበው ቆሻሻ ወደ ኃይል ይቀናበራል። አሌክሳንድሪያ ቆሻሻውን በReWorld Alexandria/Arlington Waste-To-Energy Facility በ5301 Eisenhower Avenue ያስወግዳል።

ይህ ፋሲሊቲ ቆሻሻን ወደ ኃይል በመቀየር 21 ሜጋዋት ኃይል ለማመንጨት 975 ቶን ደረቅ ቆሻሻን በማቃጠል ወደ 15,000 አካባቢ ለሚሆኑ ቤቶች ኃይል ያቀርባል።  ከተማው ቅነሳ፣ ዳግም አጠቃቀም፣ መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል እና የማዳበሪያ ቅንብርን በመከተል U.S. Environmental Protection Agency's Waste Management Hierarchy የኃይል ምለሳ ደረጃን ይከተላል።

## የቆሻሻ ዝግጅት

የእርስዎ ቤተሰብ ቆሻሻ መያዣዎች በከተማው በቀረበ የቆሻሻ መያዣ መቀመጥ እና ለእርስዎ በተመደበ የቆሻሻ ሳህን በመንገድ ጠርዝ (ወይም በቅርብ መንገድ ውስጥ) መደረግ አለበት።

### *የተከማቸ ቆሻሻ - እያንዳንዱ የመሰብሰቢያ ቀን*

በዓመቱ በየትኛውን ጊዜ በመሰብሰቢያዎ ቀን ላይ ከቆሻሻ መያዣዎ ጎን የተከማቹ እቃዎችን ማስቀመጥ ይችላሉ። የተከማቹ የብረት እቃዎች በ**Alex311**በኩል የአገልግሎት ጥያቄ ይጠይቃሉ (ለመገልገያዎች ክፍያዎች ተፈጻሚ ይደረግባቸዋል)፤ ያለበለዚያ፣ ፀደይ ይሁንም አይሁንም ትላልቅ እቃዎችን ከማንሻ ቦታዎች ያድርጉ።

## ቆሻሻ አይ

- ✕ ድንጋዮች እና አፈር
- ✕ ኤሌክትሮኒክስ
- ✕ እንደገና ሊሞሉ የሚችሉ ባትሪዎች
- ✕ አደገኛ ቁሳቁሶች
- ✕ የመታጠቢያ ቤት እቃዎች
- ✕ ጡብ እና የግንባታ እቃዎች



## *በቁጥሮች*

**21,000**
በእያንዳንዱ ሳምንት የአሌክሳንድሪያ ከተማ ቆሻሻ የሚሰበስባቸው ተቀራራቢ የደንበኞች ቁጥር።

**10,000**
ቶን የፌረስ ብረት በ2024 የበጀት ዓመት ከፕላንቱ መልሶ ተገኝቷል

**975**
ቶን የኃይል ውጋጅ በቀን

**21**
ሜጋዋት ኢነርጂ እና ኃይል ወደ 15,000 ለሚጠጉ ቤቶች መንጭቷል።



### *የግንባታ እቃዎች፣ ድንጋዮች እና ፍርስራሽ*

እንደ ፍርስራሽ፣ አለት እና ድንጋይ ያሉ ከቤት ግንባታ ፕሮጀክቶች እና የምመሬት አቀማመጥ እቃዎች የመጣ እቃ በከተማው ፕሮግራሞች ውስጥ ተቀባይነት የላቸውም። የሺንግሎች፣ የሸክላ፣ የመታጠቢያ እቃዎች፣ የደረቅ ግድግዳ እና የፍሬም ማድረጊያ እንጨት የማጓጓዣ እና የማስወገጃ አገልግሎቶች በገበያ ይገኛሉ።

እንደ የመብራት እቃዎች እና የካቢኔት እቃዎች የመሰሉ ዳግም ጥቅም ላይ የሚውሉ እቃዎችን እባክዎ ከግምት ውስጥ ያስገቡ። ለፍርስራሽ፣ አለት እና ድንጋይ ማስወገድ እባክዎ የመሬት አቀማመጥ ድርጅቶችን ያነጋግሩ። ለሌሎች አካባቢያዊ የደረቅ ቆሻሻ ፋሲሊቲዎች ዝርዝር እና ለMWCOG የገንቢ ዳግም ጥቅም ላይ የማዋል መመሪያ አገናኝ **alexandriava.gov/RefuseCollection** የሚለውን ድረገጻችንን ይጎብኙ።




# የቆሻሻ መጣያ ማዕከል

የከተማው የውጋጅ ወደ ኃይል መቀየሪያ ፋሲሊቲ ለሁሉም የአሌክሳንድሪያ ነዋሪዎች የመኖሪያ ቤት መጣያ ይገኛል። ነዋሪዎች በሳምንት አንዴ ውጋጅን ሊጥሉ ይችላሉ። ጠቅላላ የቆሻሻ፣ የፍርስራሽ ወይም የብረት ክብደት በአንድ ጉብኝት ከ500 ፓውንድ መብለጥ የለበትም። ነዋሪዎች በፎቶ ማረጋገጫ የመኖሪያ ማረጋገጫን ለማቅረብ ሊጠየቁ ይችላሉ።

*ተቀባይነት የሌላቸው እቃዎች የሚያካትቱት፦*

- *ቴሌቪዥኖች*
- *ጎማዎች*
- *አለቶች*
- *ፍርስራሽ ወይም አሸዋ*
- *በግፊት የተሞሉ ሲሊንደሮች ወይም መያዣዎች*
- *የግንባታ እና የህንጻ ፍርስራሽ*
- *አደገኛ ቆሻሻ*
- *ጥይት እና ፈንጂዎች*
- *ቁጥጥር የሚደረግበት የህክምና ውጋጅ*
- *የራዲዮአክቲቭ ወይም የጂኦሎጂካል እቃዎች*




? ጥያቄዎች አሉዎት? ReWorld ጋር በ703.370.7722 ይደውሉ

5301 Eisenhower Ave.

ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ6 a.m. እስከ 5:30 p.m., እና ቅዳሜ ከ6 a.m. እስከ 11:30 p.m.

$ ነፃ

[alexandriava.gov/RefuseCollection](alexandriava.gov/RefuseCollection)

## አካባቢያዊ ማሻሻሎች መጠናቀቅ

The Virginia Department of Environmental Quality በReWorld Alexandria/Arlington የዝቅተኛ NOx (LN®) ቴክኖሎጂ ገጠማ እና ክንውን ላይ የመጨረሻ ፈቃዶችን ሰጥቷል።

በ2022፣ ReWorld Alexandria ከውጋጅ ወደ ኃይል ፋሲልቲ በቅርብ ጊዜ ባለው ደረጃ የብክለት ቁጥጥር ቴክኖሎጂ የታቀዱ ማሻሻያዎችን አጠናቅቋል። ግቡ የናይትሮጅን ኦክሳይድ (NOx) ልቀቶችን በበለጠ በመቀነስ አካባቢን እንዲጠበቅ መርዳት ነው።

በባለቤትነት Low NOx (LN) ቴክኖሎጂ አገጣጠሙ አሁን ላይ ሲያልቅ፣ የናይትሮጅን ኦክሳይድ ልቀቶች ወደ 50% ቀንሰዋል። ጥረቱ በ ReWorld Alexandria-Arlington ፋሲሊቲ የባለብዙ ዓመት ፕሮጀክት አካል ነበር።

# ከቤት የሚወጣ አደገኛ ቆሻሻ እና ኤሌክትሮኒክስ

አንዳንድ ቤት ውስጥ ያሉ ምርቶች ማህበረሰባችን ደህንነቱ የተጠበቀ ሆኖ እንዲቆይ እንዲሁም አየራችን እና ውሃችን ንጹህ ሆኖ እንዲቆይ ልዩ ማስወገድ ይጠይቃል። እነዚህ ምርቶች ጎጂ ኬሚካሎች እና ከባድ ብረቶችን ይዟል። ከተማው ለእነዚህ እቃዎች በሳምንት ሁለት ቀን በሰራተኛ የሚከናወን መጣያ ቦታን ያንቀሳቅሳል።




3224 Colvin Street (ከDuke Street ወጣ ያለ)

ሰኞ፦ ከ7:30 am እስከ 3:30 pm (ከበዓላት በስተቀር)
ከማክሰኞ እስከ ዓርብ፦ ተዘግቷል
ቅዳሜ፦ ከ7:30 am እስከ 3:30 pm (ከበዓላት በስተቀር)
ዕሁድ፦ ተዘግቷል

$ ነፃ

alexandriava.gov/go/2703

**የቤት ውስጥ ማጽጃ ምርቶች**

**የፀረ-አረም መድኃኒቶች**

**የኤሌክትሮኒክ ውጋጅ**

**የአረም ማጥፊያዎች**

**ቀለሞች፣ ምልክቶች እና የቀለም መበጥበጫዎች**

**ሜርኩሪ የያዙ እቃዎች**
ቴርሞስታቶች፣ ቴርሞሜትሮች፣ የመብራት አምፖሎች

**የአውቶሞቲቭ ኬሚካሎች**

**የፕሮፔን ጋኖች**

**ባትሪዎች**

ባትሪዎች በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የከባድ ተሽከርካሪ እሳት ዋነኛ መነሻዎች ናቸው። ማናቸውም አይነት ቻርጅ የሚሞሉ ባትሪዎች በቆሻሻ ወይም በዳግም ጥቅም ላይ ማዋያ ውስጥ አያድርጉ። ወደ HHW ማዕከል ይውሰዷቸው። መደበኛ አልካሊን ወደ ቆሻሻ ሊጣል ሊወሰድ ይችላል።

- ሁሉም የሚሞላ ባትሪ (ለምሳሌ፦ Li-Ion, Ni-MH, Ni-Cd, Ni-Zn)
- ለአንድ ግዜ የሚያገለግል ሊቲየም (ለምሳሌ፦ የሚጫን/ሳንቲም ሴል፣ AA, AAA, 9V, C, D, CR123A, CR2)
- ሊድ አሲድ (አውቶሞቲቭ) እና የታሸገ የሊድ አሲድ



# እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል...

## ...የላቴክስ ቀለም?



በዘይት ከሚበጠበጥ ቀለም በተለየ የላቴክስ ቀለም አደገኛ ውጋጅ አይደለም እና በመደበኛ ቆሻሻ ሊወገድ ይችላል። ፈተና የሚሆነው ከቤትዎ ወደ ውጋጅ ወደ ኃይል መቀየሪያ ፕላንት ከቆሻሻ መኪናው ሳይፈስ መውሰድ ነው። ከማስወገጃ የማወፈሪያ ላቴክስ ቀለም በፊት የቀለብ መምጠጫ፣ የድመት መጸዳጃ ወይም የተቆራረጠ ወረቀትን መጨመር፣ ከዚያም መክደኛውን በመተካት ጣሳውን በፕላስቲክ መያዣ ይክደኑ። ቀለምን ወደ እቃ ማጠቢያ ወይም የጎርፍ ማስወገጃ በፍጹም አያፍስሱ! የቀለም ውጋጅን ለመቀነስ ላሉ ጠቃሚ ምክሮች፣ ገጽ 21 ላይ ይመልከቱ።



## ...የምግብ ዘይቶች፣ ቅባቶች የመኪና ቅባት?

አነስተኛ የምግብ ዘይቶች፣ ቅባቶች እና የመኪና ቅናት በወረቀጥ ሶፍት መጠረግ እና እንደ መደበኛ ቆሻሻ መጣል ይችላል። መጠነኛ መጠኖች መጠምዘዣ ባለው ክዳን ወደ መያዣው መፍሰስ እና እንደ መደበኛ ቆሻሻ መወደግ ይችላል። ለትላልቅ መጠኖች፣ ዘይቱን ወደተጠቀሙበት የዘይት መያዣ ባዶ ለማድረግ ፈቃድ ወደ ሬስቶራንት መሄድን ከግምት ውስጥ ያስገቡ። ዘይት፣ ቅባት ወይም የመኪና ዘይት በእቃ ማጠቢያ ወይም በጎርፍ ማፍሰሻ በፍጹም አያፍስሱ።

## ...በሐኪም የታዘዘ መድኃኒት?



ከተማው አላግባብ ኦፒዮይድስ ሊጠቀሙ ከሚችሉ ሰዎች እንዳይገባ በሚያደርገው ጥረት እና የእኛን ውድ የመጠጥ ውሃ አግባብ ካልሆነ የመድኃኒት መጣያነት ለመጠበቅ ይርዱ። በፍጹም መድኃኒት በሽንት ቤት ቀዳዳ አይጣሉ ወይም ውሃ አያፍስሱበት። ማንኛውም የድሮ ወይም ያልተፈለገ መድኃኒትን ዓመቱን ሙሉ በሚከተለው መጣል ይችላሉ፦

- APD ዋና መስሪያ ቤት (3600 Wheeler Avenue)
- Neighborhood Pharmacy of Del Ray (2204 Mt. Vernon Avenue)
- Inova Alexandria Hospital (4320 Seminary Road)

## ...ስለታማ ነገሮች እና መርፌዎች?



ዶክተርዎን፣ ክሊኒኩን ወይም ሆስፒታሉን በቢሯቸው ስላለው የመርፌ ወይም “የስለታማ ነገሮች” የማስወገድ ፕሮግራም ለማየት ያግኙ። ያለበለዚያ፣ መርፌዎችን፣ ስሪንጆችን፣ ላንሴቶች እና ሌሎች የተበከሉ ስለታማ ነገሮችን በማንኛውም ቀዳዳ-ተቋቋሚ፣ መልሰው ሊደፈኑ የሚችሉ፣ የሚጣል የቤት እቃ (ለምሳሌ፦ ባዶ የቤት ንጽህና ኬሚካል ጠርሙስ፣ የልብስ ማጠቢያ ሳሙና ወይም የብረት ቡና ጣሳ) ውስጥ ያስቀምጡ። “ስለታማ ነገሮች” ብለው በመያዣው ላይ ይጻፉ። መያዣው ጥቅም ላይ በዋሉ መርፌዎች ሲሞላ፣ መያዣውን በአንድ ክፍል የኬሚካል ማጽጃ ድብልቅ እና አስር ክፍል ውሃ ይሙሉ። ድብልቁን ለ20 ደቂቃ በመዘፍዘፍ ጥቅም ላይ ያዋሏቸውን ስለታማ ነገሮች ከጀርም ነጻ ያድርጉ። ከዚያም፣ ድብልቁን ወደ ማጠቢያው ላይ በማፍሰስ የማስወገጃ መያዣውን ወደ ቆሻሻው ላይ ከማስቀመጥ አስቀድሞ መክደኛውን ያሽጉ። ማጠራቀሚያውን በእርስዎ መደበኛ የቆሻሻ መጣያ ውስጥ ያስወግዱ።

## ...የሚፈነዱ ነገሮች እና ጥይት?



ርችቶች እና ፈንጂዎች ወደ ቅርብ የእሳት ጣቢያ መወሰድ አለባቸው። ጥይት ወደ ፖሊስ መምሪያ መወሰድ አለበት። የመጣያ ቦታን ለማመቻቸት የድንገተኛ ጊዜ ቁጥር ባልሆነው ስልክ እባክዎ ይደውሉላቸው። (703.746.4444).



# ባትሪዎች

አግባብነት ሳይኖራቸው ቻርጅ የሚሞሉ ባትሪዎችን መጣል በውጋጅ ኢንዱስትሪ ውስጥ የከባድ ተሽከርካሪ እሳት ከሚነሱባቸው ዋና ምክንያቶች አንዱ እንደሆነ ያውቁ ኖሯል?

ቻርጅ የሚሞሉ ባትሪዎች ወይም የአንድ ጊዜ መጠቀሚያ የሊቲየም ባትሪዎችን በመልሶ መጠቀሚያ ወይም የቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች ውስጥ አይጣሉ።

የእርስዎን ቻርጅ የሚሞሉ ባትሪዎች  (ለምሳሌ፦ Li-Ion, Ni-Cd, Ni-Mh, Ni-Zn)፣ የነጠላ አተቃቀም የሊቲየም ባትሪዎች (ለምሳሌ፦ የሚጫን/የሳንቲም ሴል, AA, AAA, 9V, C, D, CR123A, CR2) እና ከ9 ቮልት በላይ ለሆኑ ባትሪዎች በተፈቀደላቸው የመጣያ ቦታ ደህንነቱ ለተጠበቀ ማስወገድ እንዲያደርጉ ሰራተኞቻችንን በማገዝ ይቆዩ።







በከተማው ውስጥ በሻጮች በፈቃደኝነት ለቀረቡ ተጨማሪ የመጣያ ቦታዎች፣ እባክዎ **alexandriava.gov/go/3619** ላይ ይጎብኙ

## የመጣያ ቦታዎች

3224 Colvin Street (ከDuke Street ወጣ ያለ)

ሰኞ፦ ከ7:30 am እስከ 3:30 pm (ከበዓላት በስተቀር)
ከማክሰኞ እስከ ዓርብ፦ ተዘግቷል
ቅዳሜ፦ ከ7:30 am እስከ 3:30 pm (ከበዓላት በስተቀር)
ዕሁድ፦ ተዘግቷል

$ ነፃ

## የሚጣሉ ባትሪዎች ምሳሌ



ቻርጅ የሚደረጉ ባትሪዎች እርስዎ ከሚያስቡት በላይ በበርካታ ቦታዎች ይገኛሉ! እነዚህን መደበኛ እቃዎች በማንኛውም የውጋጅ መያዣዎች ውስጥ ከማስቀመጥዎ በፊት እንደፈተሹ ያረጋግጡ እና ሊያገኙ የሚችሏቸውን ማናቸውም ባትሪዎች በትክክል ያስወግዱ፦

- ገመድ አልባ የኃይል መሳሪያዎች (ለምሳሌ፦ የቅጠል መበተኛዎች፣ መብሻዎች፣ መጋዞች፣ መቁረጫዎች፣ የሳር መቁረጫዎች)
- ስልኮች፣ ገመድ አልባ ስልኮች፣ ባለሁለት መንገድ ሬዲዮኖች
- የእጅ ባትሪ
- ላፕቶፖች እና ታብሌቶች
- የባዮሜዲካል መሳሪያ
- የልጆች አሻንጉሊቶች
- የሚዘምሩ የሰላምታ ካርዶች
- ቁልፍ አልባ የመግቢያ ሪሞቶች እና ሪሞት ኮንትሮለሮች
- የኤሌክትሮኒክ ሲጋራዎች
- የኤሌክትሮኒክ የጥርስ ብሩሾች
- የጭስ አነፍናፊዎች

# የፕላስቲክ መያዣዎችን ይቀንሱ



ቀላል ክብደት ያላቸው የፕላስቲክ መያዣዎች እንደ ቆሻሻ በተለምዶ ይገኛሉ እና በካይ ሆነው ይቆያሉ። የዱር አራዊት በተለምዶ የፕላስቲክ ከረጢቶችን እንደምግብ አድርገው ይወስዱታል እና የተበላሹ የፕላስቲክ ጥቃቅን ቅንጣቶች ወደ ምግብ ሰንሰለት ውስጥ እንዲሁ እንዲገቡ ያደርጋሉ። የአሌክሳንድሪያ ከተማ ከArlington and Fairfax ካውንቲዎች ጋር ከጃንዋሪ 1፣ 2022 ጀምሮ ተግባራዊ የሆነውን የ5 ሳንቲም የፕላስቲክ መያዣ ቀረጥ ተቀብሏል።

በግሮሰሪ፣ በመገልገያ መደብሮች እና በመድኃኒት መደብሮች ሲገዙ 5 ሳንቲም የቦርሳ ክፍያን ያስወግዱ እንዲሁም በሚገዙበት ጊዜ ዳግም ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ቦርሳዎን ይዘው ይምጡ። ለበለጠ መረጃ alexandriava.gov/go/2091 ይጎብኙ

## ለ SNAP & WIC ማህበረሰቦች ዳግም ጥቅም ላይ የሚውል የመያዣ ተደራሽነት

ከተማው በሚከተለው ላይ ለ Supplemental Nutrition Assistance Program (SNAP) እና Women, Infants and Children (WIC) ማህበረሰቦች እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ቦርሳዎችን በነጻ ያቀርባል፣ አቅርቦቶቹ ሲቆዩ፦

**የማህበረሰብ እና የሰብዓዊ አገልግሎቶች የፊት ቢሮ (DCHS)**

2525 Mount Vernon Avenue

ከሰኞ - አርብ፣ 8 a.m. - 5 p.m.

**Department of Transportation & Environmental Services (T&ES)**

2900-B Business Center Drive

ከሰኞ - አርብ፣ 8 a.m. - 5 p.m.



# ከፎም የፀዳች አሌክሳንድሪያ

በ2021፣ የVirginia ጠቅላላ ጉባኤ 20 እና ከዚያ በላይ በሆኑ ቦታዎች የምግብ አቅራቢዎች የተስፋፉ የፖሊስታይሪን ምርቶች **ጁላይ 1፣ 2025** እስከ ጁላይ 1፣ 2025 ድረስ እንዳይጠቀሙ የሚከለክለውን ህግ አውጥቷል። ሌሎች ሁሉም የምግብ አቅራቢዎች እነዚህን ምርቶች እስከ **ጁላይ 1፣ 2026**እንዲያቆሙ ይጠየቃሉ።

## የተስፋፋ ፖሊስታይሪን ምንድን ነው?

Expanded polystyrene (EPS)— በተጨማሪም ፎም ወይም በተለመደው የንግድ ስም Styrofoam™ ተብሎ የሚጠራው— በነጠላ መጠቀሚያ መያዣዎች፣ ኩባያዎች፣ ሳህኖች እና ሌሎች የምግብ ማቅረቢያ ዕቃዎች ውስጥ በአብዛኛው ዳግም ጥቅም ላይ የማይውል ቁሳቁስ ነው።

## ይህ የሚተገበረው ለማን ነው?

ማንኛውም የተዘጋጀ ምግብ የሚያቀርቡ የምግብ ሻጮች የEPS ምርቶችን ለማስወገድ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው። ይህ ማለት በሚከተሉት የEPS ምርቶችን አማራጭ ምርጫዎችን ማግኘት ይጀምራሉ፦

- ሬስቶራንቶች
- ምግብ ጫኝ መኪናዎች
- የምግብ አቅራቢ ድርጅቶች
- የግሮሰሪ ማከማቻ የሳላድ ባሮች እና የተዘጋጁ የምግብ ክፍሎች
- ሌሎች የምግብ አገልግሎት ቦታዎች

## የEPS ምርቶችን ለምን ማገድ አስፈለገ?

እንደ ውጋጅ፣ የ EPS ምርቶች በቆሻሻ ማጠራቀሚያዎች ውስጥ ለመሰባበር ከ500 ዓመታት በላይ ይወስዳሉ። ባለቀላል ክብደት ቁስ ከቆሻሻ መጣያ እና ወደ አካባቢው በቀላሉ ይነፋል ይህም የውሃ መስመሮችን በመበከል ለዱር አራዊት አደገኛ ነው። የ EPS ዋና አካል የሆነው ስታይሪን በሰዎችም ላይ ከፍተኛ መጠን ሲሆን አደገኛ ሊሆን ይችላል።

## አማራጮች ምንድን ናቸው?

የEPS ምርቶችን ከመጠቀም ይልቅ፣ የሚከተለውን ይፈልጉ፦

- ዳግም ጥቅም ላይ የሚውሉ መያዣዎች
- መልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉ ፕላስቲኮች
- የቀርከሃ እና የስንዴ ገለባ
- መጠቅለያ እና ብረት

በቆሻሻ፣ በመልሶ ጥቅም ላይ ማዋል ወይም በማዳበሪያ ውስጥ አማራጮች መቀመጥ እንዳለባቸው ለመመልከት፣ "የትኛው የት ይሄዳል" የሚለውን መሳሪያ በ alexandriava.gov/ResourceRecovery ላይ ይጠቀሙ

# የበዓል ቆሻሻን መቀነስ

ከምስጋና ቀን እስከ አዲስ አመት ድረስ በአማካይ፣ የቤት ቆሻሻ ከ25% በላይ ይጨምራል። በእነዚህ ቀላል ጠቃሚ ምክሮች በበዓል ወቅት ውጋጅን ለመቀነስ እገዛ ያድርጉ።



### *ታንግለሮችን ከሰማያዊው ቆሻሻ መያዣ ያርቁ*

በዚህ የበዓል ወቅት በድጋሚ ጥቅም ላይ የሚውሉ ዕቃዎችን ማቆየትዎን እባክዎ ያስታውሱ። ሪባኖች እና የቀስት መወርወሪያዎችን ዳግም ይጠቀሙ ወይም በቆሻሻ መጣያ ውስጥ ያስቀምጧቸው።



### *ሳጥኖችን እና ካርቶኖችን ባዶ ያድርጉ፣ ያጣጥፉ እና መልሰው ጥቅም ላይ ያውሉ*

በዚህ የበዓል ወቅት የእርስዎን የመላኪያ እና የስጦታ ካርቶኖች ባዶ ማድረግ፣ ማጠጠፍ እና ወደ መልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ ማድረግ ያስታውሱ። ካርቶኖችዎን ሲያጣጥፉ በመልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ ማጠራቀሚያው ውስጥ የበለጠ ክፍተት እንዲኖር ያደርጋል።



### *እያበሰሉ መልሰው ጥቅም ላይ ያውሉ*

በዚህ የበዓል ወቅት ያበስላሉ? የወተት ካርቶኖች፣ የአሉሚኒየም ጣሳዎች እና የመጋገሪያ ሉሆች የመሰሉ እቃዎች ዳግም ጥቅም ላይ መዋል ይችላሉ። ወደቆሻሻ መያዣው ውስጥ ከመክተትዎ በፊት በውሃ መለቅለቃቸውን እና መድረቃቸውን ያረጋግጡ።




### *ተሞክሮዎችን ለመስጠት ያስባሉ*

የትእይንት ትኬቶች፣ የሁለት ሰው እራት ወይም የፊልም ኩፖኖች ምንም ፓኬጂንግ የማያስፈልጋቸው ምርጥ ሃሳቦች ናቸው። ተለዋጭ ስጦታዎች ለአካባቢ የበጎ አድራጎቶች ልገሳዎች፣ ጎዳናን እንደራስ መያዝ ወይም በአካባቢው መጠለያ ውስጥ እንስሳን ስፖንሰር ማድረግ ሊያካትቱ ይችላሉ። ትውስታዎች ከእቃዎች ይልቅ ረዥም ጊዜ ሊቆዩ እንደሚችሉ ያስታውሱ።



### *ስጦታ ዳግም ጥቅም ላይ በሚውሉ ወይም ወደጥቅም በሚቀየሩ መያዣዎች ውስጥ።*

በዚህ የበዓል ወቅት ፈጣሪ ይሁኑ! ከኦንላይን መግዣዎች ሳጥኖችን እንደስጦታ ሳጥኖች እንደገና ይጠቀሙ ወይም የነበሩ ቁሳቁሶችን እንደስጦታ መጠቅለያ ዳግም ይገልገሉባቸው። ይህ ሊያካትት የሚችለው ጋዜጦች፣ መጽሔቶች እና ከረጢቶችን ነው። ልዩ ጠቃሚ ምክር፦ ኮሚኮቹ የልጆችን ስጦታዎች ለመጠቅለል በጣም ጥሩ ናቸው።



### *በእርስዎ የበዓል ዲኮሮች የተፈጥሮ እቃዎችን ይጠቀሙ*


እውነተኛ አረንጓዴ ቦታን በመጠቀም ያስውቡ። ከበዓል በኋላ የተፈጥሮ የአበባ ጉንጉን እና አበባ ማስጌጫዎች ከሌሎች የጓሮ ቆሻሻዎ ጋር ሊበሰብሱ ይችላሉ። ማናቸውም ገመዶች፣ መብራቶች ወይም ሪበን ማስወገድዎን ያስታውሱ። የጓሮ ቆሻሻን ዳግም ጥቅም ላይ ስለማዋል ለተጨማሪ መረጃ፣ ገጽ 12 ላይ ይመልከቱ።

# የመጠቀለያ ወረቅት መመሪያ

በመልሶ ጥቅም ላይ በዋሉ እቃዎች የተሰራውን የመጠቅለያ ወረቀት ይግዙ እና የሶፍት እና የመጠቅለያ ወረቀትን ዳግም ይጠቀሙ።

የብረት እና የሚያብለጨልጭ የመጠቅለያ ወረቀት መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል እንደማይቻል ያስታውሱ።

በ **alexandriava.gov/go/4151** ላይ በዘላቂነት ለበዓላት እንዴት ማዘጋጀት እንደሚቻል የበለጠ ይወቁ



# ለመቀነስ፣ ዳግም ለመጠቀም እና መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች




## ምን የት ይሄዳል?

የትኞቹ እቃዎች መልሰው ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ወይም ወደቆሻሻ እንደሚጣሉ እርግጠኛ አይደሉም? በከተማው አዲሱ “ምን የት ይሄዳል?” መሳሪያ፣ የግምት ስራው ወጥቷል። በቀላሉ ጥያቄ ስላለዎት እቃ ስም ያስገቡ እና እንዴት በተሻለ ሁኔታ መጣል እንደሚችሉ መረጃ ይቀርባል።

alexandriava.gov/Recycling




## ከጥቅል ነጻ የሆነ ካርታ

ውጋጅን ስለመቀነስ ወይም ከጥቅል ነጻ ስለመሆን የማወቅ ጉጉት አድሮብዎት ያውቃል? ከፓኬጅ ነጻ የሆነ ላይ ጥቂት ቀላል ጠቃሚ ምክሮችን ለማወቅ እና የቤተሰብዎን የፓኬጂንግ እና የፕላስቲክ ውጋጅ ለመቀነስ ድረገጻችንን ይጎብኙ።


alexandriava.gov/go/2773



## በትክክል መልሰው ጥቅም ላይ ያውሉ የመለያ ጨዋታ

ከተማው እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ነገሮች፣ የጓሮ ቆሻሻዎች እና ቆሻሻን እንዴት ለይቶ መደርደር እንደሚችሉ የሚያስተምር የመለያ ጨዋታ ጀምሯል። የከተማ አገልግሎቶችን በመጠቀም የመደርደር እውቀትዎን ይፈትሹ እና የራስዎን ዲጂታል የአሌክሳንድሪያ ፓርክ ይገንቡ!


alexandriava.recycle.game




## ዳግም ጥቅም ላይ የማዋያ መመሪያ

ለመቀነስ እና ዳግም ለመጠቀም ይፈልጋሉ ነገር ግን የቱ ጋር እንደሚጀምሩ እርግጠኛ አይደሉም? ለእኛ አዲስ የዳግም አጠቃቀም መመሪያ የከተማውን ድረገጽ ይጎብኙ! ከሰው የተገዛ እቃን መጠገን፣ መለገስ እና መገበያየት የሚችሉባቸው የአካባቢ ሃብቶች ዝርዝርን ያግኙ።

alexandriava.gov/go/2773



## የምግብ ብክነትን ይከላከሉ

በብልሃት ለመገበያየት፣ እርስዎ ያለዎትን ምግብ መጠቀም እና ምግብን በትኩሱ ለረጅም ጊዜ ለማቆየት ባሉ ጠቃሚ ምክሮች ጋር የምግብ ብክነትን ይከላከሉ። መስተጋብር ለሚፈጥር የእራት ድግስ ማስያ፣ የእርስዎን ቀጣይ የሸያጭ ዝርዝር እንዲፈጥሩ የሚያግዝዎ ዲጂታል መሳሪያ፣ መስተጋብራዊ የማከማቻ መመሪያ እና ሌሎችንም ለመሰሉ መሳሪያዎች ለማግኘት የSave the Food ድረገጽን ይጎብኙ።

alexandriava.gov/FoodWaste

# እኛን እንዴት እንደሚያገኙ

Alex311 በተለያዩ ምቹ መንገዶች ከ175 የከተማ አገልግሎቶች በላይ ያገናኙዎታል። የAlex311 የሞባይል መተግበሪያ እና ድረገጽ ፎቶዎችን እንዲያያይዙ እና የአገልግሎት ጥያቄዎችን መገኛ እንዲገልጹ ይፈቅድልዎታል።

በአሌክሳንድሪያ ውስጥ ካለ ከየትኛውም ቦታ በ311 ወይም 703.746.4311 ላይ ይደውሉ ወይም በፌስቡክ፣ ትዊተር እና በአካል ጥያቄዎችን ያስገቡ።

አንድ የአገልግሎት ጥያቄ ሲገባ፣ የዝርዝሮች ማጠቃለያ፣ በጥያቄ አይነት ላይ በመመስረት የሚጠበቅ የምላሽ ቀን እና የጉዳይ ቁጥርን ጨምሮ ያለውን መሻሻል ለመከታተል ኢሜይል ያገኛሉ።



ALEX 311

**እርስዎን ከከተማ አገልግሎቶች ጋር ማገናኘት**

[alexandriava.gov/Alex311](alexandriava.gov/Alex311) ይጎብኙ

---

# ተገናኝተው ይቆዩ



**የከተማውን ድረገጽ በ [alexandriava.gov](alexandriava.gov) ላይ ይጎብኙ**



**በ [alexandriava.gov/ResourceRecovery](alexandriava.gov/ResourceRecovery) ላይ የኃብት ማልሶ ማግኛ ክፍል ድረገጽን ይጎብኙ**

**Follow us on social media @AlexandriaVATES**

# የበዓል ፕሮግራም

ለበዓል የክንውን ፕሮግራም፣ እባክዎ ይጎብኙ፡- [alexandriava.gov/ResourceRecovery](alexandriava.gov/ResourceRecovery)

---

# ትርጓሜዎች

የዚህን መመሪያ የስፓኒሽ ወይም የአማርኛ ስሪት ለማግኘት፣ እባክዎ የሚከተለውን ይጎብኙ፡-
[alexandriava.gov/ResourceRecovery](alexandriava.gov/ResourceRecovery)

Para leer esta guía en español, visite nuestro sitio web o use su teléfono para escanear el código QR.

ይህንን መመሪያ በአማርኛ ለማንበብ እባክዎን ድህረ ገፃችንን ይጎብኙ ወይም ስልክዎን በመጠቀም የQR ኮድን ይቃኙ።